**የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የአስቸኳይ እርዳታ ትብብር፣ ግጭቶች እና ጥቃቶች መቆም የዘላቂ መፍትሔ ጥሪ**

**ታኅሳስ 2013**

በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚቀሰቀሱ ግጭቶች፣ አለመረጋጋቶች እና የሠላም መደፍረስ ሁኔታዎች ህጻናት፣ አረጋዊያን እና የአካል ጉዳተኞችን ጨምሮ በርካታ ሴቶች ሠላምን እና ደህንነትን በመሻት ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ግጭቶቹ የወለዷቸው መጠነ ሰፊ ችግሮች በኢትዮጵያ ዜጎች፣ ንጹሃን ነዋሪዎች እና ከሌሎች ሀገራት በስደት መጥተው በተጠለሉ በርካታ ሴቶችና ህጻናት ላይ የማያባራ ስቃይ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ይህም በርካታ ህዝብ በሚኖርባቸውም አካባቢዎች ሳይቀር የምግብ፣ ውሃ፣ ባንክ የኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መሠረተ ልማት፣ ትምህርት፣ ጤናን በመሳሰሉ አቅርቦትና አገልግሎቶች መጓደል ብሎም መቋረጥ በማስከተል የራሱን አሉታዊ ጫና ፈጥሯል፡፡

ግጭት በተከሰተባቸዉ አካባቢዎች እና የአስቸኳይ ጊዜ ድጋፍ በሚሹ ቦታዎች ዓለም አቀፋዊ መርሆች ሳይሸራረፉ መተግበር እና ተፈፃሚነታቸውን መከታተል ፈታኝ በመሆኑ ፤ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች በተለይም ሴቶችና ህፃናት ለተለያዩ ጉዳቶች ተጋላጭ የመሆናቸው መጠን ከፍ ይላል። ከዚህ ቀደም ከመኖሪያቸው በተፈናቀሉ ሰዎች ላይ አተኩሮ የተሰራ ጥናት እንደጠቆመው የተጋላጭነታቸው መጠን ከፍ ብሎ በሚታይባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ አካላዊ እና ስነ ልቦናዊ፣ ፆታዊ እና ሌሎች ጥቃቶችም የመከሰት አዝማሚያ ከሌሎች የበለጠ ሆኖ ይገኛል።

በቅርቡ በኮንሶ ዞን እና አካባቢው በሚገኙት አሌ ወረዳ፣ ሰገን አካባቢ ቀበሌዎች፣ በአማሮ ወረዳ ቡኒቲ ቀበሌ እንዲሁም በደራሼ ወረዳ ጋቶ ቀበሌ በህዳር ወር ተደጋጋሚ ግጭቶች መከሰታቸውን የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ይፋ ማድረጉ ይታወሳል፡፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ብሔራዊ ክልል ሰላም እና ደህንነት ቢሮም በእነዚህ ግጭቶች ምክንያት 66 ሰዎች መሞታቸውን፣ 39 መቁሰላቸውን እንዲሁም 132, 142 ሰዎች ከመኖሪያቸው መፈናቀላቸውን ይፋ አድርጓል፡፡ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽን (UNHCR) እንዳወጣው ሪፖርት በትግራይ ክልል በተከሰተው ግጭት ምክንትያት ስለተጎዱ ዜጎች የተሟላ መረጃ ባይኖርም በትግራይ ውስጥ የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር በየቀኑ እየጨመረ መሆኑ አስጊ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ከ 53,300 በላይ ኢትዮጵያውያን ከኢትዮጵያ ወደ ምስራቅ ሱዳን ደህንነት ፍለጋ በመፍለስ በስደት ላይ እንደሚገኙም አመልክቷል። ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት በክልሉ ላለፋት ሁለት ወራት

የተቋረጡ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ተቋማት በተለይም የውሃ፣ ህክምና፣ መብራት፣ ባንክ እና መገናኛ አገልግሎቶች በሁሉም አካባቢዎች ወይም ከተሞች አገልግሎት መስጠት ባለመጀመራቸው በ በመሰረታዊ ፍጆታዎች በተለይም ምግብና ውሃ እጦት በማጋጠሙ ምክንያት ተያይዞ ለረሃብ እንዳይጋለጡ ከፍተኛ ስጋት ፈጥሯል፡፡ ከዚህ ሌላ በጥቅምት ወር በምዕራብ ወለጋ ዞን ጋዋ ቃንቃ፣ ጊላ ጎጎላ እና ሰቃ ጀርቢ ቀበሌዎችም ግድያዎች ሪፖርት ተደርገዋል። ይፋዊ መረጃዎች 32 ሰዎች እንደተገደሉ ቢያሳዩም የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የሚቾቹ ቁጥር ከዚህም ሊበልጥ እንደሚችል ጠቁሟል፡፡ኮሚሽኑ በተጨማሪም ይፋ ባደረገው ጥናት እንደተገለጸው ጥቅምት 30 ቀን 2013 ዓ.ም በትግራይ ክልል ምዕራብ ዞን፣ ሀፍታ ሁመራ ወረዳ በማይካድራ ከተማ ከ 600 በላይ ዜጎች ማንነትን መሰረት ባደረገ ኢ-ሰብዓዊ የጭካኔ ግድያ ሰለባ መሆናቸውንያመለከተ ሲሆን፣ በተከታታይ በወጡ የተለያዩ መረጃዎች መሰረትም ቁጥሩ ከዚህ በብዙ ሊበልጥ እ ንደሚችል ይገመታል።"። እንዲሁም ዜጎች በዱላ ተደብደበዋል፤ንብረታቸዉ ተዘርፏል፤ ተቃጥሏል። ይህም አሰቃቂ ክስተት ባስከተለው ፍርሃት፤ በአካባቢው ያሉ ዜጎች መኖሪያቸውን ጥለው እንደተሰደዱ ተገልጿል።

በተመሳሳይም በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል፣ መተከል ዞን ቡለን ወረዳ በኩጂ ቀበሌ ታኅሳስ 14፣2013 ዓ.ም በተፈጸመ ጥቃት ህይወታቸውን ያጡ ሰዎች ቁጥር 207 መድረሱን እና ከእነዚህ መካከል 133ቱ ወንዶች እና 35ቱ ሴቶች መሆናቸው መገለጹ ይታወሳል፡፡ ከዚህ ሌላ አንድ የ6 ወር ህፃናትን ጨምሮ 17 ልጆች እና 20 አረጋዊያን መገደላቸውም ተገልጧል፡፡ እንዲህ ያሉ በክልሉ ሰላማዊ ሰዎች ላይ የተፈፀሙ ጭካኔ የተሞላባቸው ድርጊቶች በ10 ሺህዎች የሚቆጠሩ የአካባቢው ነዋሪዎች መኖሪያቸውን ለቅቀው እንዲሰደዱ ምክንያት ሆነዋል፡፡ ማክሰኞ ታህሳስ 20 ቀን የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልልን አስመልክቶ የወጣው የቅርብ ጊዜ መረጃ እንደሚያሳየው 29, 688 ወንዶች እና 26,037 ሴቶች ከመኖሪያ ቀዬአቸዉ ተፈናቅለዋል፡፡ ይህም በአጠቃላይ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉትን ሰዎች ቁጥር ወደ 55,703 አድረሶ የነበረ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ አጠቃላይ የተፈናቃዮች ቁጥር 113,000 መድረሱን ወቅታዊ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ እነዚህ ዜጎች ለውስብስብ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰትና ቀውስ ተጋላጭነታው እየጨመረ በከፍተኛ ስጋት ላይ የሚገኙ በመሆኑ በቂ ጥበቃ እንዲሁም አስቸኳይ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ናቸው። ይህ መግለጫ ከተጠናከረበት ጊዜ በኋላም በመተከል ዞን ድባጤ ወረዳ እንደገና በሲቪል ሰዎች ላይ ጥቃት በመፈፀሙ በርከት ያሉ የንጹሃን ዜጎች ህይወት ማለፉን እናም የተፈናቀሉ ሰዎች ቁጥር መጨመሩን ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ማግኘት ችለናል።

በቅርቡ በክልሉ ከሚገኙ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጋር በተደረገ የመረጃ ልውውጥ በአካባቢው የሚገኙ ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎች ማቆያ ማዕከላት ከአቅማቸው በላይ መጠለያ ፈላጊ ሰዎችን በመቀበል ላይ እንደሚገኙ ተጠቁሟል፡፡ ከዚህም የተነሳ ለተቀበሏቸው በርካታ ሰዎች በቂ ምግብ፣ ህክምና፣ የማማከር እና የመሳሰሉ አስፈላጊና መሠረታዊ አገልግሎቶችን ለማቅረብ በእጅጉ ተቸግረዋል፡፡

በተጨማሪም በቅርቡ ከመንግስት እንዲሁም ሊሌሎች ምንጮች እንደተገኘው መረጃ በትግራይ ክልል መንግስት ያደረገው የህግ ማስከበር ስራ ከተከናወነ በኋላ በሴቶች እና ህጻናት ላይ የአስገድዶ መደፈር ጥቃት በሰፊው እየደረሰ መሆኑን እና በአከባቢው ዝርፊያ እና ሌሎች ግጭትን ትገን በማድረግ የሚፈጸሙ የሰባዊ መብት ጥሰቶች መኖረቸውን ማወቅ ተችሏል።

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ስጋትም ከችግር የተነሳ በመጠለያ ጣቢያዎች ተፋፍገው የተቀመጡ በአሥር ሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ሁኔታ ይበልጥ አሳሳቢ አድርጎታል፡፡ በጊዜያዊነት የተቋቋሙ የመጠለያ ጣቢያዎችም መሠረታዊ የሚባሉ የኮቪድ-19 መከላከያ መሳሪያዎች እና የንጽህና አገልግሎቶች የተሟሉላቸው አይደሉም፡፡ የሴቶች የጤና እና የንጽህና ፍላጎቶችን ለማሟላት እና ጤንነታቸውንም ሆነ ሰብዓዊ ክብራቸውን ለመጠበቅ አዳጋች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡ ይህም የሴቶች የጤና እና የንጽህና ፍላጎቶችን ለሚሟላት እና ጤንነታቸውንም ሆነ ሰብዓዊ ክብራቸውን ለመጠበቅ አዳጋች ሁኔታን ፈጥሯል፡፡

በኢትዮጵያ የሚገኙ የሲቪል ማህበራት ለችግሩ ምላሽ ለመስጠት እስካሁን ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች ለተጎዱ እና ለተፈናቀሉ ሰዎች በከፍተኛ ርብርብ የተቻላቸውን ድጋፍ በመስጠት ላይ ይገኛሉ። በተጨማሪም በየጊዜው ስለሚከሰቱ የሃገር ውስጥ ችግሮች እና አለመረጋጋቶች የተለያዩ ጥሪዎችን እና ጋዜጣዊ መግለጫዎችን በማውጣት ተጎጂዎች አስፈላጊውን ትኩረት እንዲያገኙና ጥቃቱም እንዲቆም ድምጻቸውን በማሰማት የማስተባበር ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ። ነገር ግን ይህ ከችግሩ ስፋት እና አንገብጋቢነት እናም አስከፊነት አንጻር አሁንም ሙሉ በሙሉ ተጎጂዎችን ለመድረስ እና እገዛ ለማድረግ አልተቻለም።

ከላይ የተጠቀሱትን አስጊ ሁኔታዎችና ቁጥሩ እየጨመረ የመጣውን ከመኖሪያው የተፈናቀለ ህዝብ ከግምት በማስገባት እኛ በስርዓተ ጾታ እኩልነት እና የሴቶችን መብት ማስከበር አላማ ይዘን የምንሰራ የሲቪል እንዲሁም ሌሎች ጉዳዩ ያሳሰበን የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከላይ የተጠቀሰውን በዜጎች ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር አስመልክቶ ለተለያዩ አካላት አስቸኳይ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

**የኢትዮጵያ መንግስት:-**

1. ለተፈጠረው ሰው ሰራሽ ችግር ተገቢ ሰብአዊ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ሀብት በአፋጣኝ እንዲያሰባስብ እና እንዲያቀርብ እንዲሁም ከሌሎች የዘርፉ ተዋናዮች ጋር በትብብር እንዲሰራ ፤
2. ሰዎች ከመኖሪያቸው እንዲፈናቀሉ ምክንያት የሆነውን በአካባቢው የተካሄዱ የግድያ ወንጀሎችና ጥቃቶች ላይ ተገቢ ምርመራ እንዲያካሂድ እና ተጠያቂነትን እንዲያረጋግጥ፣ ብሎም ጉዳት የደረሰባቸው ወገኖች ፍትህ የሚያገኙበትን እና የሚካሱበትን ሁኔታ እንዲያመቻች፤
3. ለእርዳታ ስራ እና ለክትትል ስራዎች እንዲረዳ በግጭቶች ምክንያት ህይወታቸውን ያጡ እና ቀዬአቸውን ጥለው ለተፈናቀሉ እና ጥቃት የደረሰባቸው ዜጎች ሁኔታ ወቅታዊ እና ትክክለኛ መረጃ እንዲያቀርብ፤
4. በግጭት ምክንያት የተቋረጡ ማህበራዊ አገልግሎቶች እንዲመለሱ እንዲሁም የምግብ፣ መድሃኒት፣ እናሊሌሎች አቅርቦቶች ወደህብረተሰቡ ማድረስ እንዲቻል አስፈላጊውን ትብብር እንዲያደርግ
5. ደረጃቸውን የጠበቁ ተጨማሪ መጠለያዎችን ለማቋቋም ከሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና ከበጎ አድራጎት ተቋማት ጋር በመተባበር እንቅስቃሴ እንዲያደርግ ፤
6. በመጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ ጾታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ታሳቢ ያደረጉ ጥበቃዎች መደረጋቸውን እንዲከታተል እና ተጋላጭ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች በተለይ የሴቶችና ህጻናት ደህንነት እንዲረጋገጥ ተገቢውን ሀላፊነት የመወጣት ጥረቱን አጠናክሮ እንዲቀጥል፤
7. ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ሰዎችና ተጎጂ ቤተሰቦቻቸውን ወደ መኖሪያቸዉ ለመመለስ፤ ለማቋቋም ለመከላከል፤ ለመጠበቅ እና እንዲያገግሙ ለማገዝ የሚያስችል የተቀላጠፈ እርምጃ እንዲወስድ፤
8. በግጭት አካባቢዎች ሴቶች እና ህጻናት ላይ እየደረሰ ያለው ግድያ፣ ዝርፊያ እንዲሁም የአስገድዶ መድፈር ተግባር እንዲቆም የሠላማዊ ዜጎች ግድያ እና ዝርፊያ እንዲቆም ህግን የማስከበር ሃላፊነቱን እንዲወጣ፣

9. ለተጎጂዎች ሰባዊ መብት ለማስጠበቅ እና ድጋፍ ለመስጠት የሚንቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ጥቃት እንዳይደርስባቸው አስፈላጊው ጥበቃ እንዲደረግ።

10. ህይወታቸውን ላጡ፤ አካለላቸው ለጎደለ እና ንብረታቸን ላጡ ተጎጂዎች እና ቤተሰቦቻቸው ፍትህ የሚያገኙበትን መንገድ እንዲያመቻች ጥሪ እናደርጋለን ።

<u>ዓለም አቀፍ እና ሀገር በቀል ድጋፍ ሰጪዎች፡-</u>

1. ሀብት በማሰባሰብ አስቸኳይ የምግብ፣ ውሃ፣እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች የህክምና፣ የማማከር እና ሌሎች መሠረታዊ አገልግሎቶችን የማቅረብ ስራዎችን እንዲያግዙ፣ እንዲሁም ግጭት ባለባቸው አካባቢዎች ቀደም ሲል ለሌሎች ይሰጥ የነበረውን ሌሎች የልማት ስራዎች ማስፈጸሚያ የታቀዱ የገንዘብ ድጋፎችን ወደዚህ ጉዳይ እንዲዘዋወሩ በማድረግ ተጎጂው ህብረተሰብ ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ እንዲያመቻቹ፤

2. በመጠለያ ጣቢያዎች ለሚገኙ ተፈናቃዮች ድጋፍ በማድረግ እንዲሁም መልሶ ማቋቋም በኩል የኢትዮጵያ መንግስትን እንዲያግዙ ፤

3. ከሲቪል ማህበራት እና ሌሎች ባለድሻ አካላት ጋር በመሆን ለችግሩ መፍትሄ እንዲያፈላልጉ

4. <u>የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች፡-</u>

1. በተሰማሩበት ዘርፍ ያሉ ትስስሮችን እና ሌሎች የዘርፉ ተዋናዮችን በመጠቀም ሀብት እንዲያሰባስቡና በገንዘብ እንዲሁም በአይነት ሊቀርቡ የሚችሉ ድጋፎችን እንዲያስተባብሩ፣ እንዲቀጥሉ ፤

2. ከመኖሪያቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች የማገገሚያና መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ እንዲያደርጉ ፤

3. የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ተገቢውን ክትትል እንዲያደርጉ፣ መረጃዎችንም እንዲያጠናቅሩ እንዲሁም አስፈላጊ የግፊት እና የጉትጎታ ስራዎች ላይ እንዲታትሩ ፤

4. ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶችና ህፃናት አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ማድረግ ፤

<u>የግሉ ዘርፍ፡-</u>

1. ከመኖሪያቸው የተፈናቀሉ ወገኖቻችንን ለማገዝ በዘርፉ ካሉት አካላት ጋር በመቀናጀት ርብርብ እንዲያደርግ እና ለአስቸኳይ ድጋፍ በገንዘብ እንዲሁም በአይነት ድጋፍ እንዲያደርግ ፤

2. ከጥቅም ውጪ የሆኑ መሠረተ ልማቶችን፣ መኖሪያ ቦታዎችን፣ የትምህርት እንዲሁም የጤና ማዕከላትን መልሶ ለመገንባትና ተፈናቃዮች ወደ ተለመደው ኑሯቸው ለመመለስ የሚደረገውን ጥረት ለማገዝ በሙያ፣ በሀብት እና ሌሎች ድጋፎች ላይ ተሳትፎ እንዲያደርግ ፤

3. በተለይዩ ግጭቶች ምክንያት ከፍተኛ የስለ-አእምሮ ጥቃት ለደረሰባቸው ዜጎች ሙያዊ የስነ-አእምሮና የስነ-ልቦና ድጋፍ ማግኘት እንዲችሉ በዚህ ሙያ የተሰማሩ ባለሙያዎች በተቀናጀ መልኩ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበትን መንገድ እንዲያዘጋጁ፤

**<u>ለሚዲያ ተቋማትና ባለሞያዎች፡-</u>**

1. ስለግጭቶች ብሎም ግጭቶችን ሸሽተው ስለተፈናቀ ዜጎች መረጃ አዘል የሆኑ እና የጋዜጠኝነት ስነ ምግባርን በጠበቀ መልኩ የተዘጋጁ ዘገባዎችን በየወቅቱ እንዲያቀርቡ ፤

2. በተለያዩ ምክንያቶች የተፈናቀሉ ዜጎችን ለዘገባ ቃለ መጠይቆች በሚያደርጉበት ግዜ ክብራቸውን ለመጠበቅ እና ለበለጠ ጥቃት ተጋለጭ እንዳይሆኑ ለመከላከል የሚያስችሉ ሙያዊ ጥበቃዎችን እንዲያደርጉ ፤

በተጨማሪም በግጭቶቹ ላይ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚሳተፉ አካላት በሀገራችን የተለያዩ ክፍሎችም ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ የመከላከል ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ ከአደራ ጭምር እንጠይቃለን፡፡ በሀገራችን የሚፈጠሩ ተደጋጋሚ ግጭቶችን ተከትሎ የሚስተዋሉ የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች መጨመር የተለመደ ጉዳይ እየሆነ መጥቷል፡፡ ስለዚህ ሰላማዊ እና ተጋላጭ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ከየትኛውም ወገን ከሚሰነዘር ጥቃት እና ከማንኛውም አይነት ጉዳት ለመጠበቅ በሰብዓዊ መብት ጥሰቶች ላይ ጥብቅ ክትትል እንዲሁም ትኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡ሰብአዊ መብትን ለማስጠበቅ የቁቋቋሙ መንግስታዊ እና የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የሰበአዊ መብቶች ጥሰት ላይ ክትትል እንዲያደርጉ እና ለጉዳቱ አስፈላጊውን ትኩረት እንዲሰጡት እንጠይቃለን።

እናመሰግናለን!

ከላይ የተመለከተውን መግለጫ የሰጡ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ስም ዝርዝር፡

1. Action Aid
2. Addis Ababa Women's Association (AAWA)
3. ANPPCAN-Ethiopia
4. Beza Organizing Association of Women in Need (BOAWN)
5. Civil Society Support Programme Phase 2 (CSSP2)
6. Consortium of Christian Relief and Development Association (CCRDA)
7. Ethiopian Women Lawyers Association (EWLA)
8. Ethiopian Women with Disabilities National Mass Based Association (EWDNA)
9. Family Service Association (FSA)
10. Forum for African Women Educationalists (FAWE - Ethiopia)
11. Good Samaritan Association (GSA)
12. Mesgana Child and Family Development Association
13. MujejeguwaLoka Women Development Association (MLWDA)
14. Network of Ethiopian Women's Associations (NEWA)
15. New Millennium Hope Development Organization (NMHDO)
16. Organization for Girls, Adults and Advocacy (OGGA)
17. Oxfam
18. PHE Ethiopia Consortium (PHEEC)
19. RohiWeddu Pastoral Women Development Organization
20. Setaweet
21. Siiqqee Women's Development Association
22. TIMRAN
23. Union of Ethiopian Women Charitable Association (UEWCA)
24. Voluntary Service Overseas (VSO)
25. Women Can Do It (WCDI)

NMWEO

New Millennium Women Empowerment Organization

Empowering Women | Inspiring Success

ANPPCAN-Ethiopia

WCDI

OGAA